# ለእርሻ ስራ የሚውል ገንዘብ የወጪና ገቢ አመዘጋገብ መመሪያ



## የሰሊጥ ምርትና ግብይት መረብ

## ሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ






**ማውጫ** **ገጽ**


መግቢያ........................................................................1
አቶ ሄኖክ ሰሊጥ ......................................................2

ተግባር 1: ወጪን በጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ ደብተር መመዝገብ...........................................................3

የቤተሰብ ጉልበት የዋጋ ግምት መመዝገብ.................5

ተግባር 2: ጠቅላላ ለእርሻ ስራ የሚውል ጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ መግለጫ.................................................9

ጠቅላላ የቤተሰብ ጉልበት በቀናት.............................10

ተግባር 3: ቀሪ ጥሬ ገንዘብዎን ማስላት..................................12

ተግባር 4: የትርፍ ወይም ኪሳራ ስሌት..................................13

ተግባር 5: የብድር ወለድ ወጭዎችን እና የምርት ክምችት የዋጋ ግምት መገንዘብ...........................................18

በአይነት ለተከፈሉ ምርቶች የዋጋ ግምት ማውጣት................19

የተሻሻለ ትርፍ ወይም ኪሳራ ስሌት.........................................25

ተግባር 6: የቀጣይ ምርት ዘመን ውሳኔ.................................27

ወጪዎን መመዝገብ እንዴት ይበልጥ ሊጠቅምዎት ይችላል?.29

# መግቢያ

የእርሻ ስራ ትክክለኛ የሆነ የመረጃ አያያዝና ጥንቃቄ የሚያስፈልገው የገንዘብ አስተዳደር ክህሎት የሚጠይቅ ውስብስብ ንግድ ነው።ሰሊጥ አምራች አርሶ አደር እንደመሆንዎ እርስዎም ይህንን ውስብስብ ጉዳይ ይመራሉ። እንደ መሪ ለእርሻ ተግባራት የሚያወጧቸውን ወጪዎች እንዲሁም ከእርሻ ስራ የሚያገኙትን ገቢ መከታተል ከእርስዎ የሚጠበቅ ተግባር ነው። ነገር ግን ወጭና ገቢዎን መከታተል አስቸጋሪ ሆኖ አግኝተውት ሊሆን ይችላል።

የጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ መመዝገብያ ደብተር በመጠቀም የእርሻዎን ገቢና ወጪ መመዝገብ ይችላሉ። እንደ አርሶአደር የገቢና ወጪ መመዝገብያ ደብተሩ ወደፊት ለሚወስዷቸው ውሳኔዎች መነሻ ሊሆንዎ የሚችል መሳርያ ነው። የገቢና ወጪ መዝገብ መያዝ የሚከተሉትን ጥቅሞች ያስገኝልዎታል፦

- የእርሻ ስራ እንቅስቃሴዎትን/አፈጻጸምዎን/ ለመከታተል፣
- ከእርሻ ስራዎ ያገኙትን ትርፍ ወይም ኪሳራ ለማስላት፣
- የወደፊት ዕቅድ ለማዘጋጀት/ለማቀድ፣ እና
- የእርሻ ስራዎን እንቅስቃሴ በተመለከተ ለአበዳሪ አካላት ትክክለኛ የገቢና ወጪ መረጃ በመስጠት ብድር ለመውሰድ የሚፈጀውን ጊዜ ለማሳጠር ይረዳል።

የጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ መመዝገብያ ደብተር እና ይህ የአመዘጋገብ መመርያ የእርሻ ስራዎትን ገቢና ወጪ በተደራጀ እና ግልጽ በሆነ መንገድ ለመመዝገብ ይረዳዎታል።

በዚህ መመሪያ አቶ ሄኖክ ሰሊጥ የሚባል የሰሊጥ አርሶአደር የጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጭ መዝገብ እንዴት እንደሚይዝ በምሳሌ ያሳየናል። አቶ ሄኖክ በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ የሚገኝ የሰሊጥ አምራች አርሶአደር ሲሆን ላለፉት 10 ዓመታት በዚህ ስራ ተሰማርቶ ይገኛል።

# አቶ ሄኖክ ሰሊጥ



አቶ ሄኖክ በትዳሩ ደስተኛ እና የሁለት ወጣት ልጆች አባት ነው። አቶ ሄኖክ የ5 ሄክታር የእርሻ መሬት ባለቤት ሲሆን ባለፈው ዓመት ሰሊጥ እና ማሽላ አምርቷል። ዘንድሮ የእርሻ ዘዴውን ለመቀየር አስቧል። 4ቱን ሄክታር ለማልማት፤ 1ዱን ሄክታር ግን ላለማረስ ወስኗል። 2 ሄክታር ላይ ሰሊጥ፣ 1 ሄክታር ላይ ማሽላና 1 ሄክታር ላይ ጥጥ ይዘራል።ያለውን መሬት ሙሉ በሙሉ የማያለማበት ምክንያት አምና ሰሊጡን በቅናሽ ዋጋ በመሸጡ ነው።ስለሆነም ከሰሊጥና ማሽላ በተጨማሪም ጥጥ ለመዝራት ወስኗል።

አቶ ሄኖክ ዘንድሮ ለእርሻ ስራ የሚያወጣውን ወጭና ገቢ የሚመዘግብበትን ደብተር ከህብረት ስራ ማህበሩ ሊያገኝ እንደሚችል ተገንዝቧል። ባለፈው ዓመት የገቢና ወጭ ስሌት መሰረት አቶ ሄኖክ 25,000 ብር ማትረፉን ተገንዝቧል። ከዚህ የተወሰነውን ገንዘብ ለቤት ፍጆታ ያዋለው ሲሆን ቀሪውን ለእርሻ ስራው ሊያውለው አቅዷል። አቶ ሄኖክ አምራች ጓደኞቹ አምና የነበራቸው የሰሊጥ ምርት አፈጻጸም ምን ይመስል እንደነበር ለማወቅ ጓጉቷል።

ባለፈው አመት ለእርሻ የሚያስፈልግዎትን የገንዘብ መጠን አቅደው ነበር? ገቢና ወጪዎንስ በመመዝገብ ይከታተሉ ነበር?

## ተግባር 1: ወጪን በጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ ቅጽ መመዝገብ

እርሻዎትን ማስተዳደር በወቅቱ ለእርሻ ያወጧቸውን ዝርዝር ወጪዎችን እና ከእርሻ ስራ ያገኟቸውን ገቢዎች ከመመዝገብ ይጀምራል:: ይህ በትክክል ካልተፈጸመ መረጃዎ እንዲሁም ይሄንን መረጃ መሰረት አድርገው የወሰኑት ውሳኔ የተሳሳተ ሊሆን ይችላል:: ስለሆነም የጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ መዝገብ ላይ መመዝገብ እንጀምር::

የጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ መዝገቡ ስለራስዎ እና ስለእርሻዎ አጠቃላይ መረጃ በሚመዘግቡባቸው ገጽ 2 እና 3 ላይ በሚገኙ ሁለት ሰንጠረዦች ይጀምራል:: በገጽ 4 ላይ ያለው ሰንጠረዥ በምርት ዘመኑ መጀመርያ በእጅዎ ያለው መነሻ ገንዘብና (የእራስዎ መነሻ ገንዘብ) መበደር ያሰቡት መጠን ምን ያህል እንደሆነ የሚመዘግቡበት ነው::

**ለምሳሌ**

አቶ ሄኖክ ከባለፈው ዓመት ካገኘው ትርፍ 18,000 ብር ለእርሻዉ ለማዋል የወሰነ ሲሆን ከአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም (አብቁተ) ደግሞ 16,000 ብር መበደር ይፈልጋል:: በምርት ዘመኑ መጨረሻ ተጨማሪ 5,000 ብር ከአራጣ አበዳሪ ለመበደር አቅዷል:: የአቶ ሄኖክ የገንዘብ ዕቅድ ሰንጠረዥ የሚከተለውን ይመስላል::

| የእርሻ ስራውን ለማካሄድ የታቀደ የገንዘብ ምንጭ ዕቅድ | |
|---|---|
| ምንጭ | መጠን |
| ሀ) የእራሱ መነሻ ጥሬ ገንዘብ | 18,000 |
| ለ)ከብድር | |
| ብድር 1: ከአብቁተ | 16,000 |
| ብድር 2: ከአራጣ አበዳሪ | 5,000 |
| ብድር 3: | |
| ብድር 4: | |
| ብድር 5: | + |
| ጠቅላላ ለእርሻ ስራ የታቀደ የገንዘብ መጠን = | 39,000 |

እባክዎ በጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጭ መመዝገብያ ደብተርዎ ገጽ 2፣3 እና 4 የሚገኙትን ሶስት ሰንጠረዦች ይሙሉ።

በእርሻ ወቅት ከእርሻዎ ጋር የተያያዙ ሁሉንም ገቢና ወጪዎች በጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጭ መመዝገብያ ደብተርዎ ሊመዘግቡ ይገባል። እያንዳንዱ ገቢና ወጭ አዲስ መስመር ላይ ይመዘገባል። ይህንን ከገጽ 8 እስከ 43 ባሉት ሰንጠረዦች መመዝገብ ይችላሉ። ጥሬ ገንዘብ ገቢ በሚለዉ በአምስተኛዉ ረድፍ በመጀመሪያዉ መስመር ማለትም ሚያዝያ ወር ላይ መነሻ ገንዘብህን መዝግብ።

እነዚህ ሰንጠረዦች እያንዳንዳቸው ስድስት ረድፎች የያዙ ሲሆን በመጀመርያው ረድፍ ገንዘቡ ወጭ/ገቢ የተደረገበት ቀን፣ በሁለተኛው ረድፍ የእርሻ ሥራ ዝርዝር፣እርስዎ ወይም የቤተሰብዎ አባል እርሻ ሥራዉ ላይ ከዋለ/ከዋሉ የዋሉበት የቀን ብዛት በሶስተኛዉ ረድፍ 'የቤተሰብ ጉልበት በቀን' በሚለዉ ይመዘገባል፣ ስራዉ ለአንድ ወይም ከአንድ በላይ ለሆኑ ሰብሎች ተሰርቶ ሊሆን ይችላል፤ስለሆነም በአራተኛው ረድፍ 'የሰብልዓይነት' በሚለዉ የሰብሉ ዓይነት ይመዘገባል፤ በአምስተኛው ረድፍ 'ጥሬ ገንዘብ ገቢ' እንዲሁም በስድስተኛው ረድፍ 'ጥሬ ገንዘብ ወጭ' የምንመዘግብባቸው ናቸው። የተዘረዘረው ተግባር ገንዘብ የሚያስገኝ ከሆነ የገንዘብ መጠኑ በአምስተኛው ረድፍ ከ'ጥሬ ገንዘብ ገቢ' ስር የሚመዘገብ ሲሆን የተዘረዘረው ተግባር ገንዘብ የሚያስወጣ ከሆነ ግን የገንዘብ መጠኑ በስድስተኛው ረድፍ ከ'ጥሬ ገንዘብ ወጭ' ስር ይመዘገባል። በእያንዳንዱ ወር መጨረሻ የወጭና ገቢ እንዲሁም ስራ ላይ የዋለ የቤተሰብ ጉልበት በቀናት ንዑስ ድምር አስልተው ያስቀምጡ።

ማሳሰብያ፡- የእርሻ ሥራው በቤተሰብ ጉልበት የተሰራ ከሆነ በተግባር ለሰራተኛ ወጭ አይወጣም። ስለሆነም ለቀን ሰራተኛ በሚከፈል የቀን ክፍያ ተመን በስድስተኛዉ ረድፍ አይመዘገብም።

ገጽ 5 ላይ ወጭ ሊያስወጡ ወይም ገቢ ሊያስገኙ የሚችሉ የእርሻ ተግባራት ተዘርዝረዋል። በተጨማሪም ከአንድ ዓመት በላይ ሊገለገሉባቸው የሚችሉ የእርሻ መሳርያዎች- ለምሳሌ መጥረብያ፣ ማጭድ ወይም መኮትኮቻ ወ.ዘ.ተ.ሲገዙ ወጭውን መመዝገብያ ደብተሩ ላይ መመዝገብዎን ያረጋግጡ።

ማሳሰብያ፡- ብድር ሲያገኙ፣ እንስሳ ሸጠው ወይም አከራይተው ያገኙትን ገቢ ለእርሻዎ ካዋሉት በገቢ ስር ሊመዘግቡት ይገባል (በ5ተኛ ረድፍ 'ጥሬ ገንዘብ ገቢ' ስር) ።

## የቤተሰብ ጉልበት መመዝገብ



እርስዎ ወይም የቤተሰቡ አባላት እርሻው ላይ ተሳታፊ ሆነው የእርሻ ስራው ቢሰራም በተጨባጭ ገንዘብ ወጪ አይሆንም። ለዚህ ስራ የቀን ሰራተኛ ቀጥረው ቢሆን ኖሮ ሰራተኞቹን ሊከፍሉ ይገደዱ ነበር። በዚህ መሰረት ትክክለኛ የእርሻ ምርት ማምረቻ ወጪዎችን ለማወቅ እርስዎ ወይም የቤተሰቡ አባላት እርሻው ላይ ለምን ያህል ሰዓታት እንደሰሩ ሊመዘግቡ ይገባል። ለስራ የዋለ የቤተሰብ ጉልበት ሲመዘገብ የተሰራዉ የእርሻ ስራ በረድፍ ሁለት ሲመዘገብ፤እርስዎ ወይም የቤተሰብዎ አባል ከዚህ ስራ ላይ የዋሉት የቀን ብዛት በረድፍ ሦስት ይመዘገባል። በዚህ ጊዜ 'ጥሬ ገንዘብ ገቢ' እና 'ጥሬ ገንዘብ ወጭ' የሚሉት ረድፎች አይሞሉም።እርስዎ እና የቤተሰብዎ አባላት በወሩ የሰሩት ጠቅላላ ቀናት በእያንዳንዱ ወር በሦስተኛዉ ረድፍ መጨረሻ የሚመዘግቡበት በጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ መመዝገብያ ደብተሩ ላይ ያገኛሉ።

ምሳሌ

ሚያዝያ 5 ቀን 2010 ላይ አቶ ሄኖክ ማሳውን ለማጽዳት 2,000 ብር ለሰ
ገዛ:: በተጨማሪም በዚሁ እለት ለሰሊጥ ለመጠቀም የአፈር ማዳበርያ በ
ካቀደው በታች 14,000 ብር ብድር አገኘ:: አቶ ሄኖክ ግንቦት 25 ቀን
የመጀመሪያ እርሻ አረሰ:: ለዚህም 2,400 ብር ከፈለ:: አቶ ሄኖክ በእርሻ

አቶ ሄኖክ የተዘረዘሩትን ተግባራት የጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ መመዝገቢ

| 1. ሚያዝያ 2010 | | |
|---|---|---|
| ቀን | የተግባር ዝርዝር | የቤተሰብ ጉልበት በቀን |
| ሚያዝያ 1/ 2010 | የእራሱ መነሻ ጥሬ ገንዘብ | |
| ሚያዝያ 5/ 2010 | የሰራተኛ ወጪ ማሳ ለማጽዳት | |
| ሚያዝያ 18/ 2010 | የዘር ግዥ | |
| ሚያዝያ 18/ 2010 | የአፈር ማዳበሪያ ግዥ | |
| | | |
| | 1.የሚያዝያ የቤተሰብ ጉልበት ቀናት ንዑስ ድምር= | 0 |

ጽ 10-13 የጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ መመዝገቢያ ደብተሩ ላይ እንደሚ

| 2. ግንቦት 2010 | | |
|---|---|---|
| ቀን | የተግባር ዝርዝር | የቤተሰብ ጉልበት በቀን |
| ግንቦት 10/ 2010 | ከአብቁተ የተገኘ ብድር | |
| ግንቦት 25/ 2010 | የመጀመሪያ እርሻ በሬ ኪራይ | |
| ግንቦት 25/ 2010 | የመጀመሪያ እርሻ | 4 |
| | | |
| | 2. የግንቦት የቤተሰብ ጉልበት ቀናት ንዑስ ድምር = | 4 |

ራተኞች ከፈለ:: ከ13 ቀናት በኋላ 6 ኪሎ አባሲና የሰሊጥ ዘር በ330 ብር 5,000 ብር ገዛ:: አቶ ሄኖክ ግንቦት 10 ቀን 2010 ዓ.ም ላይ ከአብቁተ 2010 ዓ.ም በሬዎች ተከራይቶ ሰሊጥና ማሽላ የሚዘራበትን መሬቱን ዉ ወቅት ከሚስቱ ጋር በመሆን ሁለት ሙሉ ቀን ስራዉ ላይ ዉሏል::

ያ ደብተሩ ገጽ 8 - 9 ላይ እንደሚከተለው መዝግቧል::

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የሰብል ዓይነት | ጥሬ ገንዘብ ገቢ | ጥሬ ገንዘብ ወጪ |
| | | 18,000 | |
| | ሰሊጥ፣ማሽላ እና ጥጥ | | 2,000 |
| | ሰሊጥ | | 330 |
| | ሰሊጥ | | 5,000 |
| | | + | + |
| | 1. የሚያዝያ ንዑስ ድምር = | 18,000 | 7,330 |

ከተለው አስፍሯል

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የሰብል ዓይነት | ጥሬ ገንዘብ ገቢ | ጥሬ ገንዘብ ወጪ |
| | ሰሊጥ፣ማሽላ እና ጥጥ | 14,000 | |
| | ሰሊጥ እና ማሽላ | | 2,400 |
| | ሰሊጥ እና ማሽላ | | |
| | | + | + |
| | 2. የግንቦት ንዑስ ድምር = | 14,000 | 2,400 |

የመዝገብ አያያዝ አንኳር መርሆዎች የሚከተሉት ናቸው:

- እያንዳንዱን ገቢና ወጭ መመዝገብ
- በትክክል መመዝገብ
- ወጥነት/ተከታታይነት ባለው መልኩ መመዝገብ
- ዝርዝር/ጥልቅ መረጃ መመዝገብ

ያስታውሱ፡- ትክክለኛ የሆነ የትርፍና ኪሳራ ስሌት ለማግኘት እያንዳንዱ ገቢ የሚያስገኝ እና ወጭ የሚያስወጣ የእርሻ ተግባር ሙሉ በሙሉ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡ ስለዚህ ሁሌም በቤተሰብ ጉልበት ሲያሰሩ፤ገንዘብ ሲቀበሉና ወጭ ሲያደርጉ የጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጭ መመዝገብያ ደብተር ላይ መመዝገብዎን ያረጋግጡ፡፡

ማሳሰብያ፡-ይህ የጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጭ መዝገብ የእርሻ ስራዎን ገቢና ወጪ ብቻ የሚመዘግቡበት ስለሆነ፣ ለቤት ፍጆታ የዋሉ የምግብ፣ የልብስ ወይም ሌሎች ተዛማጅ ወጪዎችን ሊመዘግቡበት አይገባም፡፡ ገንዘብ ገቢ አድርገው ከሆነ ለእርሻ ስራ ያሰቡትን መጠን ብቻ በጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጭ መዝገቡ ላይ ያስፍሩ፡፡

መልካም እድል! ድጋፍ ወይም እገዛ ካስፈለገዎ እባክዎትን የቅርብ ተጠሪውን ያነጋግሩ፡፡



## ተግባር 2: ጠቅላላ ለእርሻ ስራ የሚውል ጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ መግለጫ

ባለፈው ዓመት የተሻለ ገቢ/ገንዘብ ያገኙበትን ወር ያስታውሳሉ?

ቀጣዩ ተግባር አጠቃላይ ያገኙትን ገንዘብ እና ያወጡትን ወጪ በማጠቃለል የጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ (የጥሬ ገንዘብ ፍሰት) መግለጫ ማዘጋጀት ነው:: መግለጫውን የሚያዘጋጁት የእያንዳንዱን ወር ንዑሳን ድምር ወደ ገጽ 46 በመውሰድ ነው::

ለምሳሌ

አቶ ሄኖክ ወደ ገቢና ወጪ መመዝገብያ ደብተሩ በመመለስ ከገጽ 8-43 በገጾቹ መጨረሻ ላይ የሚገኝ የእያንዳንዱን ወር የጥሬ ገንዘብ ገቢና ጥሬ ገንዘብ ወጪ ንዑስ-ድምር ተመለከተ:: እነዚህ ንዑሳን ድምሮች በገጽ 46 በሚገኘው የገቢና ወጪ ሰንጠረዥ አሰፈረ::

| 13. የጥሬ ገንዘብ ፍሰት መግለጫ | | |
|---|---|---|
| ንዑሳን-ድምሮች | ጥሬ ገንዘብ ገቢ | ጥሬ ገንዘብ ወጪ |
| 1. ሚያዝያ | 18,000 | 7,330 |
| 2. ግንቦት | 14,000 | 2,400 |
| 3. ሰኔ | | 8,520 |
| 4. ሀምሌ | | 8,990 |
| 5. ነሐሴና ጳጉሜ | | 1,600 |
| 6. መስከረም | | 1,100 |
| 7. ጥቅምት | 45,200 | 32,824 |
| 8. ህዳር | 8,400 | 1,000 |
| 9. ታህሳስ | 0 | 8,392 |
| 10. ጥር | 2,100 | 5,767 |
| 11. የካቲት | | |

| | | |
|---|---|---|
| 12. መጋቢት | 20,680 + | 5,366 + |
| ድምር = | ሀ. 108,380 | ለ. 83,289 |

መጨረሻ መስመር ላይ ያሉ ጠቅላላ ጥሬ ገንዘብ ገቢና ጥሬ ገንዘብ ወጪ ለማግኘት ከ ቁ.1-12 ቁልቁል ይደምሯቸው፡፡

አሁን ገጽ 46 ላይ የሚገኘውን ሰንጠረዥ 13 በመጠቀም የእርሻዎትን የጥሬ ገንዘብ ፍሰት መግለጫ ያዘጋጁ፡፡

## ጠቅላላ የቤተሰብ ጉልበት በቀናት

የእርሻዎትን የጥሬ ገንዘብ ፍሰት መግለጫ ካዘጋጁ በኋላ የቤተሰብ ጉልበት ማጠቃለያ መግለጫ ማዘጋጀት ይኖርብዎታል፡፡ ይህንንም የሚያዘጋጁት በየወሩ መጨረሻ ያሰሉትን የቤተሰብ ጉልበት በቀናት ንዑስ ድምሮችን አንድ ሰንጠረዥ ላይ በማስፈር ነው፡፡

ምሳሌ


አቶ ሄኖክ አልፎ አልፎ ከወንድሙ ወይም ሚስቱ ጋር በመሆን እርሻው ላይ ይሰራል፡፡ የሰሩባቸውን ጠቅላላ ቀናት በየወሩ ይመዘግባል፡፡ አቶ ሄኖክ ወደ ገቢና ወጪ መመዝገብያ ደብተሩ በመመለስ ከገጽ 8-43 በገጾቹ መጨረሻ የሚገኙ የእያንዳንዱን ወር የቤተሰብ ጉልበት በቀናት ንዑሳን-ድምሮችን በመውሰድ ገጽ 47 ላይ በሚገኘው ሰንጠረዥ ቁጥር 14 ላይ አሰፈረ፡፡

| 14. የቤተሰብ ጉልበት በቀናት | |
|---|---|
| 1. ሚያዝያ | 1 |
| 2. ግንቦት | 4 |
| 3. ሰኔ | 5 |
| 4. ሀምሌ | 2 |
| 5. ነሐሴና ጳጉሜ | 2 |
| 6. መስከረም | 1 |

| | |
|---|---|
| 7. ጥቅምት | 2 |
| 8. ህዳር | 1 |
| 9. ታህሳስ | 0 |
| 10. ጥር | 0 |
| 11. የካቲት | 0 |
| 12. መጋቢት | 0 |
| ሐ. ጠቅላላ የቤተሰብ ጉልበትድምር በቀናት = | 18 |

መጨረሻ መስመር ‘ሐ` ያለው ጠቅላላ የቤተሰብ ጉልበት ቀናት ለማስላት አቶ ሄኖክ ከ1-12 ያሉትን ቀናት ቁልቁል ደመራቸው:: በዚህ መሰረት ከወንድሙ እና ሚስቱ ጋር ሆነው የሰሩባቸው ቀናት በጠቅላላው 18 ናቸው::

አሁን ገጽ 47 ላይ ባለው ሰንጠረዥ ቁጥር 14ን በመጠቀም
የቤተሰብ ጉልበት ቀናትን ድምር ያስሉ::





## ተግባር 3: ቀሪ ጥሬ ገንዘብዎን ማስላት

**ከነበረዎት መነሻ ጥሬ ገንዘብ ጋር ሲነጻጸር መጨረሻ ላይ ያለዎት ቀሪ ጥሬ ገንዘብ ይበልጣል ወይስ ያንሳል?**

ያገኙትን ገቢና ያወጡትን ወጭ ካሰሉ በኋላ እንዳተረፉ ወይም እንደከሰሩ ማወቅ ይችላሉ:: ይሄንን ማወቅ የሚችሉት የገንዘብ ፍሰት የማጠቃለያ መግለጫ በሰንጠረዥ 15 መሰረት ካዘጋጁ ነው::

**ምሳሌ**

**አቶ ሄኖክ ማትረፋን ወይም መክሰሩን ማወቅ ይፈልጋል:: ይህንን ለማወቅ በጥሬ ገንዘብ ወጪና ገቢ መመዝገብያ ደብተሩ ገጽ 48 ላይ በሚገኘው ሰንጠረዥ 15 ይጠቀማል:: በወቅቱ ያገኘውን ጥሬ ገንዘብ ገቢ ደመረ (=ሀ. ጠቅላላ ጥሬ ገንዘብ ገቢ ከሰንጠረዥ 13- ይህ ማለት ከእራስዎ ያወጡትን መነሻ ጥሬ ገንዘብ ይጨምራል) ከዚህ በመቀጠል በወቅቱ ያወጣውን ወጪ ቀነሰ (ለ. ጠቅላላ ጥሬ ገንዘብ ወጪ ከሰንጠረዥ 13). በዚህ መሰረት የአቶ ሄኖክ ቀሪ ጥሬ ገንዘብ 25,091 ብር ነው:: ስለዚህ ገቢው ከወጪው ይበልጣል::**

| 15. የማጠቃለያ ሚዛን መግለጫ | |
|---|---|
| ሀ. ጠቅላላ ጥሬ ገንዘብ ገቢ | 108,380 |
| ለ. ጠቅላላ ጥሬ ገንዘብ ወጪ | 83,289 - |
| ሐ. ቀሪ ጥሬ ገንዘብ = | 25,091 |

የእርሻዎን ቀሪ ጥሬ ገንዘብ ለማስላት በጥሬ ገንዘብ ወጪና ገቢ መመዝገብያ ገጽ 48 የሚገኘውን ሰንጠረዥ 15 ይጠቀሙ::

አቶ ሄኖክ ቀሪ ጥሬ ገንዘቡ ከመነሻ ጥሬ ገንዘቡ ስለበለጠ ደስተኛ ነው:: ነገር ግን የቤተሰብ ጉልበትና የቋሚ ንብረት አገልግሎት/የእርጅና ተቀናሽ ሳያሰሉ ትክክለኛ ትርፍና ኪሳራን ማወቅ አይቻልም:: ትርፍ/ኪሳራ እንዴት እንደሚሰላ ቀጥለን እናያለን::

## ተግባር 4: የትርፍ ወይም ኪሳራ ስሌት

**የባለፈው ዓመት ትርፍ ወይም ኪሳራ ሲያሰሉ የቤተሰብ ጉልበትና የቋሚ ንብረት አገልግሎት ተቀናሽ ግምት ውስጥ አስገብተዋል?**

ከእርሻ ስራ ማትረፍ ወይም አለማትረፍዎን ለማወቅ የጥሬ ገንዘብ ፍሰት ብቻ ማየት በቂ አይደለም:: ለምሳሌ ትራክተር ቢገዙ ሊያገኙ ከሚችሉት ገቢ በላይ ወጪ ሊያደርጉ ይችላሉ:: በሌላ በኩል የቤተሰብ ጉልበት በመጠቀምዎ ምክንያት ጥሬ ገንዘብ ወጪ ባለማድረግዎ ወጪዎ ትንሽ ሊመስልዎ ይችላል:: ነገርግን ትርፍ ወይም ኪሳራ በትክክል ለማወቅ የአገልግሎት/የእርጅና ተቀናሽ እና የቤተሰብ ጉልበት ማስላት አለብዎት::

በመጀመርያ የቤተሰብ ጉልበት በገንዘብ መተመን ያስፈልጋል:: የቤተሰብ ጉልበት በገንዘብ ለመተመን በአካባቢዎ የነበረ አማካይ የሰራተኞች የቀን ክፍያ በመውሰድ በጠቅላላ የቤተሰብ ጉልበት ቀናት ማባዛት ይችላሉ:: በተለያየ ወራት የነበረዉ የሰራተኛ ዋጋ ሊለያይ ይችላል ሆኖም ግን አማካኙን መዉሰድ ይገባል:: የቤተሰብ ጉልበት የገንዘብ ግምት ለማስላት ሰንጠረዥ 16ን ይጠቀሙ::

**ለምሳሌ**

አቶ ሄኖክ፤ሚስቱ እና ወንድሙ ለ18 ቀናት እርሻው ላይ ሰርተዋል:: በወቅቱ የነበረው የሰራተኞች የቀን ክፍያ ዝቅተኛው 80 ብር ከፍተኛው ደግሞ እስከ 120 ብር ይደርስ ነበር:: ስለዚህ አቶ ሄኖክ የቤተሰብ ጉልበት በገንዘብ ለመገመት በወቅቱ የነበረውን አማካይ የሰራተኞች ክፍያ 100 ብር በቀን ሂሳብ በ18 የቤተሰብ ጉልበት ቀናት አባዛ::

| 16. ጠቅላላ የቤተሰብ ጉልበት ዋጋ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| መ. ጠቅላላ ድምር የቤተሰብ ጉልበት ቀናት | | ብር/ቀን | | ሰ. ጠቅላላ የቤተሰብ ጉልበት ዋጋ |
| 18 | X | 100 | = | 1,800 |

ሁለተኛ የገዙት ትራክተር፣ በሬ፣ አህያ ከነጋሪው (ካሮ) ወይም ሌሎች ቋሚ ንብረቶች ለአንድ ክረምት ብቻ የሚጠቀሙባቸው አይደሉም:: ስለሆነም ለእነዚህ አይነት ቋሚ ንብረቶች ያወጡት ወጪ በሙሉ በአንድ ዓመት የትርፍ ወይም ኪሳራ መግለጫ ውስጥ ማካተት የለብዎትም:: ወጪዎቹ የቋሚ ንብረቶቹን የአገልግሎት ዘመን ግምት ውስጥ በማስገባት በተከታታይ ዓመታት የትርፍ ወይም ኪሳራ መግለጫ ከፋፍለው ማካተት ይኖርብዎታል:: በዓመቱ ለእርሻ አገልግሎት የተገዙ ቋሚ ንብረቶች ማጠቃለያ መግለጫ ለማዘጋጀት ሰንጠረዥ 17ን ይጠቀሙ:: ይህ ሰንጠረዥ የወቅቱን ትርፍ ወይም ኪሳራ ለማስላት/ለማዘጋጀት ይጠቀሙበታል::

ምሳሌ:- አቶ ሄኖክ ጥቅምት ወር ላይ የመጀመርያ ሰሊጡን በሸጠ በማግስቱ ጥንድ በሬ ገዛ:: በሬዎቹን ለብዙ አመታት እንደሚጠቀምባቸውም ተገነዘበ:: የበሬዎቹን ግዢ እንደሚከተለው ሰንጠረዥ 17 ላይ መዘገበ::

| 17. በዓመቱ ለእርሻ አገልግሎት የተገዙ ቋሚ ንብረቶች | |
|---|---|
| የተገዙ ቋሚ ንብረቶች | ዋጋ |
| 1. በሬዎች | 18,000 |
| 2. | |
| 3. | |
| 4. | |
| 5. | |
| 6. | + |
| ጠቅላላ የተገዙ ንብረቶች ዋጋ = | 18,000 |

የቋሚ ንብረት አገልግሎት/እርጅና ተቀናሽ ለማስላት የንብረቱ መግዣ ዋጋ በአመታዊ አገልግሎት ተቀናሽ ድርሻ በመቶኛ(%)

በማባዛት ሰንጠረዥ 18 ላይ ይመዝግቡ:: ለእያንዳንዱ ቋሚ ንብረት አመታዊ አገልግሎት ተቀናሽ ድርሻ በመቶኛ (%) ያለው ሲሆን የአገልግሎት ተቀናሽ ለማስላት ይረዳዎ ዘንድ እንደሚከተለው ቀርቧል::

| የንብረት አይነት | አገልግሎት ተቀናሽ | | የንብረት አይነት | አገልግሎት ተቀናሽ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ዓመት/ ዘመን | ዓመታዊ ድርሻ | | ዓመት/ ዘመን | ዓመታዊ ድርሻ |
| ትራክተር | 15 | 0.07 | ማጭድ | 2 | 0.50 |
| በሬ | 8 | 0.13 | መጥረብያ | 3 | 0.33 |
| ማረሻ | 4 | 0.25 | ዶማ | 3 | 0.33 |
| ማረሻ (የትራክተር) | 10 | 0.10 | የምግብ ማብሰያ | 2 | 0.50 |
| ግመል | 5 | 0.20 | የኬሚካል መርጫ | 4 | 0.25 |
| አህያ | 5 | 0.20 | ባርኔጣ/ ኮፍያ | 3 | 0.33 |
| ጋሪ | 4 | 0.25 | የውሃ ማቆርያ | 2 | 0.50 |
| የትራክተር ተሳቢ | 10 | 0.10 | ሞፈርና ቀምበር | 4 | 0.25 |

**ማስታወሻ:-** ከላይ ከተጠቀሱት ቋሚ ንብረቶች ሌላ ከገዙ የአገልግሎት/ የእርጅና ተቀናሽ ለማስላት የቅርብ ተጠሪዎን ያማክሩ::

አንድ ቋሚ ንብረት የአገልግሎት ዘመኑ ሲያበቃ ሌላ ንብረት በመግዛት ይተካል ተብሎ ይታሰባል:: ንብረቱን የአገልግሎት ዘመኑ ቢያበቃም ሊጠቀሙበት ይችላሉ:: ነገር ግን የአገልግሎት ዘመኑ ላበቃ ንብረት ቢጠቀሙበትም የአገልግሎት/የእርጅና ተቀናሽ ሊያሰሉ አይገባም:: ዓመታዊ አገልግሎት ተቀናሽ ለማስላት የሚከተለውን ቀመር ይጠቀሙ፡-

ቀመር፡ የዓመታዊ አገልግሎት/የእርጅና ተቀናሽ ድርሻ በመቶኛ (%) = 1 ÷ የግልጋሎት ዘመን(አመት)

አቶ ሄኖክ ቀመሩን በጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ መመዝገቢያ ደብተሩ ላይ በሚገኘው ሰንጠረዥ 18 በመታገዝ የአገልግሎት/የእርጅና ተቀናሽ እንዴት እንደሚያሰላ ያሳየናል።

ምሳሌ:- አቶ ሄኖክ 3 ቋሚ ንብረቶች ተጠቅሟል፤ የገዛቸው በሬዎች፣ ከ3 አመት በፊት የገዛው አህያ እና ከ2 አመት በፊት የገዛው ጋሪ። ሶስቱም ንብረቶች የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈ ስላልሆነ የአገልግሎት/ የእርጅና ተቀናሽ አስልቷል። አቶ ሄኖክ በጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጭ መመዝገቢያ ደብተሩ ገጽ 50 እና 51 ላይ በሚገኘው ሰንጠረዥ 18 የአገልግሎት/የእርጅና ተቀናሽ ወጪውን አስልቶ እንደሚከተለው አስፍሯል።

| 18. የአገልግሎት/የእርጅና ተቀናሽ ወጭ | | | |
|---|---|---|---|
| የቋሚ ንብረቶች ዝርዝር | የመግዣ ዋጋ | ዓመታዊ የአገልግሎት ተቀናሽ ድርሻ | ዓመታዊ የአገልግሎት ተቀናሽ ወጭ |
| 1. በሬዎች | 18,000 | × 0.13 = | 2,340 |
| 2. አህያ | 4,500 | × 0.2 = | 900 |
| 3. ጋሪ | 4,000 | × 0.25 = | 1,000 + |
| ረ.ጠቅላላ አመታዊ የአገልግሎት ተቀናሽ ወጭ= | | | 4,240 |

የአቶ ሄኖክ ጠቅላላ አመታዊ የአገልግሎት ተቀናሽ ወጭ ድምር 4,240 ብር ነው።

የቤተሰብ ጉልበት ካልተጠቀሙ እና ቋሚ ንብረት በዓመቱ ካልገዙና ከበፊት ከሌለዎት ሰንጠረዥ 16፣17 እና 18ን ላይጠቀሙባቸው ይችላሉ።ካልተጠቀሙባቸው- ሰንጠረገሮቹ ላይ 0 ይጻፉ። የሰንጠረዥ 16፣ 17 እና 18 ውጤት ትርፍዎን ወይም ኪሳራዎን ሲያሰሉ ሰንጠረዥ 19 ላይ ይመዘግባሉ።

ከዚህ በፊት በነበሩ ተግባራት ትርፍ ወይም ኪሳራዎን ለማስላት ጠቃሚ የሆኑ ሁሉንም ቁጥሮችን ለይተዋል:: ቀጣዩ ተግባር እነዚህን ቁጥሮች በጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ መመዝገብያ ደብተርዎ ገጽ 52 ላይ በሚገኘው ሰንጠረዥ 19 ላይ በማስፈር ማስላት ነው:: የሚከተለው ምሳሌ ትርፍ ወይም ኪሳራ ለማስላት የትኞቹ ቁጥሮች እንደሚያስፈልግዎ ያሳያል::

ምሳሌ:- አቶ ሄኖክ የጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ መመዝገብያ ደብተሩን ተመልሶ በመመልከት ትርፍ ወይም ኪሳራ ለማስላት የሚጠቅሙ ቁጥሮችን እንደሚከተለው አስፍሯል::

| 19. ትርፍ ወይም ኪሳራ | |
|---|---|
| መ. ቀሪ ጥሬ ገንዘብ (ገጽ 48 ይመልከቱ) | 25,091 |
| ዐ. መነሻ ጥሬ ገንዘብ (ገጽ 4 ይመልከቱ) | 18,000 - |
| ሠ. ጠቅላላ የቤተሰብ ጉልበት ዋጋ (ገጽ 48 ይመልከቱ) | 1,800 - |
| ንዑስ-ድምር | 5,291 |
| ጠቅላላ የተገዙ ንብረቶች ዋጋ (ገጽ-49 ይመልከቱ) | 18,000 + |
| ረ. ጠቅላላ አመታዊ የአገልግሎት ተቀናሽ ወጭ (ገጽ 51 ይመልከቱ) | 4,240 - |
| ትርፍ ወይም ኪሳራ = | 19,051 |

አቶ ሄኖክ ቀሪ ጥሬ ገንዘቡ ከመነሻ ጥሬ ገንዘቡ በ7,091 ብር እንደሚበልጥ ያሳየው ነበር:: ነገር ግን የቤተሰብ ጉልበት ዋጋ እና በወቅቱ የተገዙ የቋሚ ንብረቶች ጠቅላላ ዋጋ ሲጨምርበት የወቅቱ ትርፍ ከ19,000 ብር በላይ ሆኖ አግኝቶታል::

በዚህ መሰረት የእርሻ ስራዎን ትርፍ ወይም ኪሳራ በጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ መዝገብዎ ሰንጠረዥ 19 ላይ ማስላት ይችላሉ::

## ተግባር 5: የብድር ወለድ ወጭዎችን እና የምርት ክምችት የዋጋ ግምት መገንዘብ

ባለፈው አመት ለወሰዱት ብድር ወለድ አስልተው ነበር?
ከባለፈው አመት የተከማቸ ምርት አለዎት?

ከፍተኛ የጥሬ ገንዘብ ወጭ ከሚያስወጡ አበይት የእርሻ ተግባራት አንዱ የብድር ወለድ ክፍያ ነው:: የከፈሉት የወለድ መጠን ምን ያህል እንደሆነ በግልጽ ለማወቅ የወሰዱትን ብድር እና የመለሱትን የብድር መጠን የጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጭ መዝገብ ገጽ 53 ያለው ሰንጠረዥ ቁጥር 20 ላይ በመመዝገብ ያቀናንሱ::

ምሳሌ:- አቶ ሄኖክ በጠቅላላው 16,100 ብር ለአብቁተ ብድር ይመልሳል:: ያስታውሱ የወሰደው ብድር 14,000 ብር ነበር:: በእርሻው ወቅት የገንዘብ እጥረት ስለገጠመው 4,000 ብር ከአራጣ አበዳሪ ተበድሮ የመለሰው 8,000 ብር ነው:: በተጨማሪም በሼል 3 ኩንታል ሰሊጥ በ3,500 ብር ሸጠ:: የአቶ ሄኖክ የወለድ ስሌት የሚከተለውን ይመስላል::

| 20. የብድር ወለድ ወጭ | | | |
|---|---|---|---|
| የተከፈለ ብድር | የተወሰደ ብድር | የተከፈለ ወለድ | |
| የብድር ምንጭ 1: አብቁተ | | | |
| 16,100 - | 14,000 | = | 2,100 |
| የብድር ምንጭ 2: ህጋዊ ያልሆነ አበዳሪ | | | |
| 8,000 - | 4,000 | = | 4,000 |
| የብድር ምንጭ 3: ህጋዊ ያልሆነ አበዳሪ | | | |
| 3,500 - | 3,500 | = | 0 |
| የብድር ምንጭ 4: | | | |
| - | | = | |
| የብድር ምንጭ 5: | | | |
| ጠቅላላ የተወሰደ ብድር = | 21,500 + | = | |
| ጠቅላላ የተከፈለ ወለድ= | | | 6,100 + |

## በአይነት ለተከፈሉ ምርቶች የዋጋ ግምት ማውጣት

እስካሁን ጥሬ ገንዘብዎን፣ የአገልግሎት/የእርጅና ተቀናሽ፤ የቤተሰብ ጉልበት እና የብድር ወጭዎን በጥንቃቄ አይተዋል። ነገር ግን በግልጽ ያልታየ በአይነት (በሰብል ምርት) የተከፈለ የእርሻ ወጪ ሊኖር ይችላል። ለምሳሌ ኮብራሪ (የእርሻ አስተዳዳሪ) ለሰራው ስራ ማበረታቻ ከተሰበሰበው ምርት የተወሰነ ኩንታል ሊሰጡት ይችላሉ ወይም በ`ሼል` ስምምነት ለወሰዱት ብድር በስምምነቱ መሰረት የተወሰነ ኩንታል ሰሊጥ ሊከፍሉ ይችላሉ።

ሰሊጡን በሼል ለወሰዱት ብድር ባይከፍሉት ምርቱን ምን ሊያደርጉት ይችሉ እንደነበር ያስቡ። በእርግጠኝነት ሰሊጡን ሊሸጡት እና ገቢ ሊያገኙበት ይችሉ ነበር። ሰሊጡን በአይነት በመክፈልዎ ከሰሊጥ ሽያጭ ሊያገኙት ይችሉ የነበረውን ገቢ አጡ ማለት ነው። በሌላ አነጋገር ለተቀባዩ በሰሊጡ የወቅቱ ዋጋ ከፈሉ ማለት ነው። የጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ መዝገብ ላይ የሚገኙ ሰንጠረዥ ቁጥር 21 እና 22 በአይነት የተከፈለውን ያልተስተዋሉ ወጭ ለማስላት ይረዱዎታል። አቶ ሄኖክ እንዴት እንዳሰላው ቀጥሎ ያሳየናል።



**ምሳሌ**

**አቶ ሄኖክ ምርቱን ከመሰብሰቡ በፊት በሼል 3 ኩንታል ሰሊጥ በ3,500 ብር ለኩንታል ሒሳብ ሽጧል፡፡ ስለሆነም በሼል የወሰደውን ብድር በሰሊጥ መክፈል ነበረበት፡፡ በተጨማሪም የተወሰነ ማሽላ ለቀን ሰራተኞች ለምግብ ሰጥቷል፡፡ አቶ ሄኖክ በአይነት ወጪ የተደረጉ ምርቶችን በገጽ 54-55 ሰንጠረዥ ቁጥር 21 ላይ እንደሚከተለው መዝግቧል፡፡**

| 21. በአይነት የተከፈሉ ወጪዎች | | |
|---|---|---|
| ቀን | የወጪ ዝርዝር | መለኪያ |
| ሰኔ 15/ 2010 | እርሻ ላይ ለሰሩ የቀን ሰራተኞች የተሰጠ ማሽላ | ኪሎ |
| ጥቅምት 16/ 2010 | የተወሰደ 3,500 ብር ብድር ለመክፈል የተሰጠ ሰሊጥ | ኩንታል |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

አቶ ሄኖክ ከነጋዴ ለወሰደው 3,500 ብር ብድር መመለሻ 3 ኩንታል ሰሊጥ ሰጠ። ሰሊጡን ለነጋዴው በሚያስረክብበት ወቅት የሰሊጥ ዋጋ 2,800 ብር ለኩንታል ነበር።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ብዛት | | የአንዱ ዋጋ | | ጠቅላላ ዋጋ |
| 50 | × | 35 | = | 1,750 |
| 3 | × | 2,800 | = | 8,400 |
| | × | | = | |
| | × | | = | |
| | × | | = | + |
| በዓይነት የተከፈሉ ወጭዎች ጠቅላላ የዋጋ ግምት = | | | | 10,150 |

ሰንጠረዥ 21 በአይነት የተከፈለ ምርት በተጨባጭ ወጪ የተደረገው በገንዘብ ምን ያህል እንደሆነ ያሳያል:: ሰሊጥዎን ሳይሰበሰብ በሼል መልክ ከሸጡ ሰንጠረዥ 21 ላይ የተመለከተውን በአይነት የተከፈለ ምርት የወለድ መጠን አያሳይም:: ሰንጠረዥ 22 በአይነት ለተከፈለ ብድር ወለድ ለማስላት ይረዳዎታል:: አቶ ሄኖክ እንዴት እንዳሰላ ለመረዳት በሚቀጥለው ገጽ ማየት ይችላሉ::

ምሳሌ
አሁን አቶ ሄኖክ ለብድር መክፈያ የሰጠውን 3 ኩንታል ሰሊጥ የዋጋ ግምቱ 8,400 ብር እንደሆነ ያውቃል:: ነገር ግን በተጨባጭ በዚህ ፈንታ ያገኘው 3,500 ብር ብቻ ነው:: አቶ ሄኖክ በአይነት ከከፈለው ግምት ዋጋ ላይ የወሰደው ብድር ሲቀንስ በተዘዋዋሪ የወለድ ወጪው 4,900 ብር ሆኖ አግኝቶታል::

| 22. በአይነት የተከፈሉ ብድሮች የወለድ ወጪዎች | | |
| --- | --- | --- |
| በአይነት የተከፈለ ምርት የዋጋ ግምት | የተወሰደ የብድር መጠን | በአይነት የተከፈለ ብድር የወለድ መጠን |
| 8,400 | - 3,500 | = 4,900 |
| | - | = |
| | - | = |
| | - | = + |
| በአይነት የተከፈለ ብድር ጠቅላላ የወለድ መጠን = | | 4,900 |

ባለፈው አመት በአይነት የከፈሉትን ብድር የሚያስታውሱ ከሆነ ሰንጠረዥ 21 ላይ ማስፈር ይችላሉ:: በመቀጠልም የጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ መዝገብ በገጽ 56 ሰንጠረዥ ቁጥር 22ን በመጠቀም ማስላት ይችላሉ::

የብድር ወጪዎን መጠን ካወቁ በኋላ በመቀጠል ያልተሸጠና በክምችት ያለ የምርት መጠን ማወቁ ጠቃሚ ነው፡፡ ምርቱ በቀጣይ ቢሸጥ ገቢ ሊያስገኝ እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

በክምችት ያለውን የምርት መጠን ለማወቅ ከተሰበሰበው ጠቅላላ የምርት መጠን ላይ የተሸጠ፣ ለምግብ ፍጆታ የዋለ እና በሼል ለተወሰደ ብድር የተከፈለበት ምርት መጠን መቀነስ ይችላሉ፡፡ ቀሪ የክምችት መጠን ለማወቅ የጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ መዝገብ ገጽ 57 ላይ ያለው ሰንጠረዥ ቁጥር 23 ይጠቀሙ፡፡

ምሳሌ

አቶ ሄኖክ በአጠቃላይ የሰበሰበው ምርት 16 ኩንታል ሰሊጥ፣ 20 ኩንታል ማሽላ ና 20 ኩንታል ጥጥ ነው፡፡ ከሰበሰበው የሰሊጥ ምርት 3 ኩንታል በሼል ለወሰደው ብድር በአይነት የከፈለ ሲሆን 13 ኩንታል ተሸጧል፡፡ በተጨማሪም የሰበሰበውን የጥጥ ምርት ሁሉንም ሸጦታል፡፡ ከሰበሰበው የማሽላ ምርት 12 ኩንታል የሸጠ ሲሆን 2 ኩንታል ደግሞ ለምግብ ፍጆታ አውሏል፡፡ ቀሪውን ምርት በቀጣይ ሊሸጠውም ለምግብነት ሊያውለውም ይችላል፡፡

| 23. የምርት ክምችት መጠን | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ኩንታል | | | | |
| የሰብል ዓይነት | የተሰበሰበ የምርት መጠን | | የተሸጠ + ለምግብ ፍጆታ የዋለ + በአይነት የተሰጠ/ ለብድር የተከፈለ | | ቀሪ ክምችት |
| 1. ሰሊጥ | 16 | - | 16 | = | 0 |
| 2. ማሽላ | 20 | - | 14 | = | 6 |
| 3. ጥጥ | 20 | - | 20 | = | 0 |

አቶ ሄኖክ በክምችት የቀረው ምርት 6 ኩንታል ማሽላ ብቻ ነው፡፡

ቀሪዉን ክምችት በቀጣይ የሚሸጡት ከሆነ ተጨማሪ ገቢ ያስገኝልዎታል ማለት ነዉ፡፡ ጠቅላላ ቀሪ ክምችትን በሰብሉ ዓይነት የመሸጫ ዋጋ በማባዛት የቀሪ ክምችት የዋጋ ግምትን ማወቅ ይቻላል፡፡

ለምሳሌ

አቶ ሄኖክ 6 ኩንታል የማሽላ ክምችት አለዉ፡፡ የአንድ ኩንታል የማሽላ የመሸጫ ዋጋ 2,000 ብር ሲሆን፤ አቶ ሄኖክ የማሽላ ክምችቱን በመሸጫ ዋጋ ሲያባዛዉ 12,000 ብር ሊሸጥ የሚችል ምርት እንዳለዉ ማወቅ ችሏል፡፡

| 24. የተከማቸ ምርት ዋጋ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ወደፊት ሊገኝ የሚችል ገቢ | | | | |
| የሰብል ዓይነት | በክምችት ያለ | | የመሸጫ ዋጋ/በኩንታል | | ጠቅላላ ዋጋ |
| 1. ሰሊጥ | 0 | × | 3,500 | = | 0 |
| 2. ማሽላ | 6 | × | 2,000 | = | 12,000 |
| 3. ጥጥ | 0 | × | 2,000 | = | 0 |
| ሰብሉ ቢሸጥ ወደፊት ሊገኝ የሚችል ገቢ= | | | | | 12,000 |

## የተሻሻለ ትርፍ ወይም ኪሳራ ስሌት

እስካሁን ባሉት ተግባራት የብድር ወጭዎን ማለትም የወለድ ወጭና በዓይነት ለተደረጉ ክፍያዎች ያሉትን ወጭዎች ለይተዋል፡፡ እንዲሁም በክምችት ያለ ምርትን ዋጋ አዉቀዋል፡፡

በአጠቃላይ እነዚህ በኋላ የተሰሉ ወጭዎችን በማካተት የእርሻ ስራ አፈጻጸምዎ በፊት ሰንጠረዥ 19 ላይ ከተገኘዉ ትርፍና ኪሳራ ስሌት ጋር ማወዳደር ይችላሉ፡፡ የትርፍ/ ኪሳራ መግለጫዎን ለማሻሻል ገጽ 59 ላይ የሚገኘውን ሰንጠረዥ ቁጥር 25 መጠቀም ይችላሉ፡፡

ምሳሌ
አቶ ሄኖክ ከዚህ በፊት ያሰላዉን ትርፍና ኪሳራ ስሌት ሰንጠረዥ 19 ላይ አስተዋለ፤ ከዛ ያገኘዉን ትርፍ/ኪሳራም በሰንጠረዥ 25 የመጀመሪያ መስመር ላይ አምጥቶ ሞላ፡፡ በመቀጠልም በሰንጠረዥ 21 እና 22 ያሰላቸዉን በዓይነት የተከፈሉ ወጭዎች የዋጋ ግምትና የወለድ ወጭዎችን በማምጣት ካሁን በፊት ካገኘዉ ትርፍ/ኪሳራ ላይ ቀነሳቸዉ፡፡ እነዚህ ወጭዎችም በፊት የነበረዉን ትርፍ/ኪሳራ ይቀንሱታል፡፡በመጨረሻም በክምችት ያለ ምርት ዋጋን ማለትም ሰንጠረዥ 24ን በመጨመር የተሻሻለ ትርፍ/ኪሳራ ለማወቅ ችሏል፡፡

በዚህ መሰረት ሰንጠረዥ 25ን በመጠቀም የተሻሻለ የትርፍ ወይም ኪሳራ መግለጫ አዘጋጅ፡፡

| 25. የተሻሻለ ትርፍ ወይም ኪሳራ ስሌት | |
|---|---|
| ትርፍ/ኪሳራ (ሰንጠረዥ 19 ይመልከቱ) | 19,051 |
| ብድር ያልሆኑ በዓይነት የተከፈሉ ወጭዎች ጠቅላላ ዋጋ (ሰንጠረዥ 21 ይመልከቱ) | 1,750 - |
| በአይነት የተከፈለ ብድር ጠቅላላ የወለድ መጠን (ሰንጠረዥ 22 ይመልከቱ) | 4,900 - |
| ሰብሉ ቢሸጥ ወደፊት ሊገኝ የሚችል ገቢ (ሰንጠረዥ 24 ይመልከቱ) | 12,000 + |
| የተሻሻለ ትርፍ ወይም ኪሳራ ስሌት = | 24,401 |

ምሳሌ

አቶ ሄኖክ ሰንጠረዥ 25ን ሲመለከት፤ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ በዓይነት ለተከፈሉ ወጭዎች አዉሏል። በዓይነት ለተከፈሉ ወጭዎች 1,750 እና በዓይነት ለተከፈሉ ወጭዎች ወለድ 4,900 በአጠቃላይ በ6,650 ብር ትርፉን ዝቅ አድርገዉታል። እንደ ዕድል ሆኖ ግን በክምችት ያለዉ ሰብል የዋጋ ግምት የተሻሻለ ትርፉን ካሁን በፊት ካሰላዉ ትርፍ በላይ አሳይቶታል።

የተሻሻለ ትርፍ/ኪሳራ ስሌት:

- የተለያዩ የብድር ወጭዎችን እንድናወዳድር ያግዘናል
- በዓይነት የሚደረግ የብድር ስምምነትን የዋጋ ተመን እንድንረዳ ያስችለናል
- ለምግብ ፍጆታ የዋሉና በክምችት ላይ ያሉ ምርቶችን የዋጋ ግምት እንድናዉቅ ያስችለናል
- ወደ እዉነት የተጠጋ የእርሻችን ትርፋማነት እንድንገመግም ያችለናል

## ተግባር 6: የቀጣይ ምርት ዘመን ውሳኔ

**የባለፈውን አመት የወጪና ገቢ መዝገብ መሰረት በማድረግ ለቀጣይ አመት ያቅዳሉ?**

ለቀጣይ የምርት ዘመን ሲያቅዱ መረጃን መሰረት ያደረገ ውሳኔ በመወሰን አደጋን መቀነስ ይችላሉ:: የገንዘብ ገቢና ወጪዎን በጥሬ ገንዘብ መዝገብ ላይ ማስፈር ለቀጣይ የምርት ዘመን የጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ መጠን ለመገመት ያስችልዎታል:: አቶ ሄኖክ የገቢና ወጪ መዝገቡን መሰረት በማድረግ ለቀጣይ እንዴት እንደሚያቅድ ቀጥሎ ይገልጽልናል::

ምሳሌ:- አቶ ሄኖክ 25,091 ብር በኪሱ ይዟል:: ባለፈው አመት ህጋዊ ካልሆኑ አበዳሪዎች ባይበደር ገንዘቡ ከዚህ በላይ ይሆንለት ነበር:: ለሚቀጥለው የምርት ዘመን አሁን ካለው ገንዘብ የተወሰነውን ለመጠቀም አስቧል:: እቅዱን በተጨባጭ ለማስቀመጥ አቶ ሄኖክ የጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ መመዝገብያ ደብተሩ ሰንጠረዥ 26 ላይ አስፍሯል::

- አቶ ሄኖክ የባለፈው አመት የገንዘብ ፍሰት መግለጫውን በየወሩ ሲመለከት እስከ ጥቅምት ወር ምንም አይነት ከሽያጭ ያገኘው ገቢ እንዳልነበረ ይገነዘባል:: በተጨማሪም ከምርት ዘመኑ መጀመርያ ምርት መሸጥ እስኪጀምር ባለው ጊዜ በቂ ገንዘብ ማግኘት እንዳለበት ያውቃል::
- ከሚያዝያ 2010 እስከ መስከረም 2011 ያወጣው ወጪ 29,940 ብር ነው:: ገቢውን በትኩረት ሲመለከት ጥቅምት 16 ላይ ሰሊጡን ሸጧል:: ከጥቅምት 1 እስከ 15 ባለው ጊዜ 6,824 ብር ተጨማሪ ወጪ አውጥቷል:: ከሽያጭ በፊት የነበረው ወጪ 36,764 ብር ነበር::
- ባለፉት አመታት የማምረቻ ወጪ እየጨመረ በመምጣቱ ምክንያት ሽያጭ  እስኪጀምር ድረስ ባለው ጊዜ ወጪው

42,000 ብር ሊደርስ እንደሚችል ገምቷል፡፡

- አቶ ሄኖክ ካለው 25,091 ብር ለሚቀጥለው የምርት ዘመን 15,000 ብር ሊቆጥብ አቅዷል፡፡.
- አሁን አቶ ሄኖክ ለቀጣይ የምርት ዘመን የሚያስፈልገውን ጠቅላላ የብድር መጠን ለመገመት በጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ መዝገቡ ላይ በሚገኘው ሰንጠረዥ ቁጥር 26 እንደሚከተለው ሞልቷል፡፡

| 26. የቀጣይ የምርት ዘመን ውሳኔ | | |
|---|---|---|
| | የዘንድሮን እንቅስቃሴ/ አፈጻጸም ይመልከቱ | መጠን |
| 1. የቀጣይ ምርት ወቅት የወጪ ግምት (ከሽያጭ በፊት) | ከሰንጠረዥ 1-12 ይመልከቱ (ገጽ 8-43)<br>ሰንጠረዥ 13 ይመልከቱ (ገጽ 46) | 42,000 |
| 2. ለቀጣይ የእርሻ ወቅት የሚቆጠብ ገንዘብ | ሰንጠረዥ 15 ‘ሐ’ ን ይመልከቱ (ገጽ 48) | 15,000<br>- |
| 3. ጠቅላላ የሚያስፈልግ የብድር መጠን ግምት = | | 27,000 |

አቶ ሄኖክ አምና የወሰደው ብድር 21,500 ብር ነበር፡፡ ዘንድሮ ግን ተጨማሪ ገንዘብ እንደሚያስፈልገው በመገንዘቡ ከአብቁተ 20,000 ብር ከህብረት ስራ ማህበሩ ደግሞ 5,000 ብር ሊበደር አቅዷል፡፡ ቀሪውን 2,000 ብር ከዘመድ/ጓደኛ ወይም ህጋዊ ካልሆነ አበዳሪ ለመበደር ይሞክራል፡፡

የቀጣይ የምርት ዘመን እቅድዎን ለማቀድ የጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ መዝገብ ገጽ 60 ላይ በሚገኘው ሰንጠረዥ 26ን ይጠቀሙ፡፡

## ወጪዎን መመዝገብ እንዴት ይበልጥ ሊጠቅምዎት ይችላል?

“ሞኝና ወረቀት የያዘውን አይለቅም”

“በቃል ያለ ይረሳል በጹሑፍ ያለ ይወረሳል”

በአጠቃላይ አበዳሪ ተቋማት የተሻለ የማበደር ፍላጎት የሚኖራቸው ገቢና ወጪዎን በግልጽ ማቅረብ ሲችሉ ነው:: ስለዚህ የጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ መዝገብዎ ከህጋዊ አበዳሪ ተቋማት ለመበደር ሊያግዝዎት ይችላል::

የጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ መዝገቡ ወርሃዊ የጥሬ ገንዘብ ወጪዎን መጠን በግልጽ ሊያሳይዎት ይችላል:: በተጨማሪም የትኛው ወር ላይ ከፍተኛ ወጪ እንዳወጡ አስልተው ማወቅ ይችላሉ:: በዚህ መረጃ መሰረት በሚቀጥለው የምርት ዘመን በየወሩ የሚስፈልግዎትን የገንዘብ መጠን ለማቀድ እና በዕቅዱ መሰረት እርሻዎትን ለማስተዳደር ያግዝዎታል::

በተጨማሪም የእርስዎን ገቢና ወጪ መዝገብ ከሌሎች አቻ አርሶአደሮች መዝገብ ጋር ቢያነጻጽሩ የተሻለ ይጠቅምዎታል:: ከሌሎች አርሶአደሮች ጋር በማነጻጸር ከፍተኛ ወጪ ያስዎጣዎትን የእርሻ ተግባር መለየት ይችላሉ:: በተጨማሪም በመወያየት ወጭ መቀነስ የሚቻልበትን መንገድ በመለየት በጋራ መጠቀም ይቻላል::









አድራሻ፡- ቤኔፊት-ኤስ ቢ ኤን

ጎንደር ግብርና ምርምር ማዕከል


ፖ. ሣ. ቁ 1337 ቀበሌ 16

ጎንደር ኢትዮጵያ

Website: www.sbnethiopia.org

E-mail: sbnethiopia@gmail.com








ወጪ
ገቢ